ETHIOPIA COMMODITY EXCHANGE
የኢትዮጵያ ምርት ገበያ

## ጋዜጣዊ መግለጫ

ለበለጠ መረጃ አቶ ጥላሁን በቀለን በtilahun.bekele@ecx.com.et 0911 40 34 02 ወይም 0115 54 70 01 ያግኙ::

# ደወሉ ለሰሊጥ ተደወለ: ኢ.ሲ.ኤክስ የሰሊጥ ግብይት መጀመሩን አስታወቀ

**አዲስ አበባ** - አንደኛ ዓመቱን እያከበረ ባለበት ወቅት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ኢ.ሲ.ኤክስ የሰሊጥ ግብይት ሚያዝያ 26 ቀን 2001 ዓ.ም እንደሚጀምር አስታወቀ፡፡

ዋነኛ የሰሊጥ አምራች አገር እንደመሆኗ ኢትዮጵያ በአለምአቀፍ የሰሊጥ ግብይት ውስጥ ከቻይና ፣ህንድ እና በርማ ቀጥሎ በአራተኛ ደረጃ ትገኛለች፡፡ ኢትዮጵያ ሁሉንም የሰሊጥ ምርቷን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የምትታወቅ ሲሆን ባለፉት ጥቂት አመታት ወደውጭ የምትልከው የሰሊጥ ምርት በፍጥነት እያደገ በአሁኑ ወቅት በመሪነት ከሚገኙት ሁለት አገሮች አንዷ ሆናለች፡፡ ኢትዮጵያ የሰሊጥ ምርቷን በዋናነት የምትልክባቸው አገራት ቻይና፣ ጃፓን፣ ኮርያ ፣እስራኤል እና ቱርክ ናቸው፡፡

ሰሊጥ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያለው አስተዋፅኦ በፍጥነት እያደገ ነው፡፡ ባለፉት ሶስት አመታት ወደ ውጭ የተላከው የሰሊጥ ምርት እና ያስገኘው ገቢ ከቀደሙት አመታት ጋር ሲነፃፀር በቅደም ተከተላቸው የ435% እና 807% እድገት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ባላት አመቺ የአየር ፀባይ በመታገዝ ምርጥ የሰሊጥ አይነቶችን ብታመርትም ከግብይት ስርአታችን ድክመቶች የተነሳ ከሰሊጥ በበቂ ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም፡፡ የአገር ውስጥ የሰሊጥ ግብይት ካሉበት ተግዳሮቶች አንዱ የክፍያ ውል ማፍረስ ሲሆን ይህም ሻጮችን ክፍያቸውን ለማግኘት ለወራት እንዲቆዩ አስገድዷቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከጥራት እና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ያሉት ችግሮች አገሪቱ በአለም አቀፍ ግብይት ያላትን ስም እና ዝና እያጉደፈ ይገኛል፡፡ ሌላኛው የዘርፉ ችግር ምንም አይነት የዋጋ ጨረታ ስርዓት ያለመኖር ሲሆን ይህም የዋጋ አወጣጥ ሂደቱን እጅግ የተንዛዛ እና አስተማማኝ ያልሆነ አድርጎታል፡፡

የሰሊጥ የአገር ውስጥ ግብይት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል መሆኑ የተጠቀሱትን ተግዳሮቶች ለመፍታት  የሚያስችል አስፈላጊ አዲስ ግኝት በመሆኑ የኢትዮጵያ የጥራጥሬ፣ ቅባት እህሎች እና ቅመማ ቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር ያለውን ድጋፍ አስታውቋል። በተያያዘም የማህበሩ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙሴ ያዕቆብ የሚከተለውን ተናግረዋል፡ “እንዲህ አይነት ሀላፊነት የሚወስድ እና ፍትሀዊ የግብይት ስርዓት የሚያሰፍን ተቋም እንዲጀመር ከጠየቅን 14 — 15 አመት ይሆነናል። ኢ.ሲ.ኤክስ እኛ ከጠበቅነው በላይ መስራት ይችላል።”

ኢ.ሲ.ኤክስ የሰሊጥ ማከማቻ መጋዘኖች በሁመራ፣ ጐንደር፣ እና ነቀምት የከፈተ ሲሆን እንዲሁም በቀጣይ ተጨማሪ መጋዘን በመተማ የሚከፍት ሲሆን፤ ግብይቱ በኢ.ሲ.ኤክስ የግብይት መድረክ በየቀኑ የሚካሄድ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት የሰሊጥ የምርት ወቅት እያለፈ እንደመሆኑ ግብይቱ አሁን መጀመሩ ኢ.ሲ.ኤክስ የሚሰጠውን የገበያ ጥቅሞች በማሳየት በሚቀጥለው የምርት ወቅት ማለትም ከጥቅምት ወር ጀምሮ ለሚኖረው ከፍተኛ መጠን ያለው የሰሊጥ ምርት ግብይት ዝግጅት ይሆናል።

**ኢ.ሲ.ኤክስ. ለገበያ እድገት፤ ለአገር እድገት።** www.ecx.com.et